የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የሳምንታዊ መረጃ ማሰራጫ

# ሳምንታዊ የቢዝነስ መረጃዎች

*(ሐምሌ 8- 15/2016 ዓ.ም)*
July 15- July 22/2024

**በኮሙኒኬሽንና ህዝብ ግንኙነት መምሪያ የሚዘጋጅ**

## 1. ዕልባት ያገኘው የንግድ ምክር ቤቱ ፕሬዚዳንትና አመራሮች ምርጫ

ንግድ ምክር ቤቶች ከተቋቋሙበት አዋጅና ከመተዳደሪያ ደንብ ውጪ ሳይካሄድ የቆየው የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ጠቅላላ ጉባዔና ምርጫ ከስድስት ዓመታት በኋላ ሐሙስ ሐምሌ 11 ቀን 2016 ዓ.ም. ተካሂዷል፡፡

**ሪፖርተር ጋዜጣ፡ *July 21, 2024***

አቶ ሰብሰብ ፕሬዚደንት የሆኑት 81 ድምፅ በማግኘት ነው፡፡ ከእሳቸው ጋር ለፕሬዚዳንትነት የተወዳደሩት የአማራ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት አቶ አሰፋ ዓለምነው ደግሞ 40 ድምፅ አግኝተዋል፡፡ ሦስተኛዋ ተወዳዳሪ የነበሩት የአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ወ/ሮ መሰንበት ሸንቁጥ 17 ድምፅ አግኝተዋል፡፡

አቶ ሰብሰብ ላለፉት ሰባት ዓመታት ንግድ ምክር ቤቱን በፕሬዚዳንትነት ሲመሩ ከቆዩት መላኩ ዕዘዘው (ኢንጂነር) ኃላፊነቱን ተቀብለው 23ኛው ፕሬዚዳንት ሆነዋል፡፡

https://www.ethiopianreporter.com/131606/

## 2. በከበ ማዕድናት እሴት መጨመር ቀዳሚው ድርጅት

በከበሩ ማዕድናት የበለጸገችው ኢትዮጵያ እንደ ኦፓል፣ ኢምራልድና የመሳሰሉ ማእድናትን ለውጭ ገበያ በማቅረብ የውጭ ምንዛሬ ታገኛለች፡፡ ይሁንና ማእድናቱ ለውጭ ገበያ የሚቀርቡበት መንገድ ሀገሪቱን በሚፈለገው ልክ ተጠቃሚ አዳላደረጋትም፡፡ ከኢትዮጵያ ይልቅ ማእድናቱን በጥሬው የሚቀበሉ ሀገሮችና ሕገወጦች የበለጠ ተጠቃሚ እንደሆኑ ይገለጻል፡፡

**ኢትዮጵያ ፕረስ ድርጅት፡ July 19, 2024**

እነዚህ ማዕድናትም በተለምዶ ከወርቅ ያነሰ ዋጋ እንዳላቸው ተደርገው ይቆጠራሉ፤ እንደ ሀገርም ብዙ ትኩረት ሳይሰጣቸው እንደቆዩ የዘርፉ ባለሙያዎች ይናገራሉ፡፡ ብዙዎች እንደሚሉት ዘርፉ ገና ብዙ ያልተሠራበት፣ የሠለጠነ የሰው ኃይልና ቴክኖሎጂ የሚፈልግ ነው፡፡ ሌሎች ብዙ ተግዳሮቶች ያሉበትና ችግሮቹን ለመፍታትም ብዙ መሥራትን የሚጠይቅ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት በዘርፉ ተሠማርተው እየሠሩ ያሉ ጥቂት ተቋማትም ቢሆኑ በሚፈለገው ልክ ለውጥ ማምጣት አልቻሉም፡፡

https://press.et/?p=132466

## 3. ኢትዮጵያና የተባበሩት አረብ ኤሜሬቶች በራሳቸውን ገንዘብ ለመገበያየት ተስማሙ

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ባወጣው መግለጫ ፥ ስምምነቱን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ገዥ ማሞ ምህረቱ እና የተባበሩት አረብ ኤሜሬቶች ብሔራዊ ባንክ ገዢ ካሊድ ሞሃመድ ባላማ ፈርመዋል፡፡

**ፋና፡ ሐምሌ 9፣ 2016**

በዚህም በሁለቱ ሀገራት ለሚደረግ ግብይት የራሳቸውን ገንዘብ ማለትም ድርሃምና ብር ለመጠቀም ነው ስምምነት ላይ የደረሱት፡፡

https://www.fanabc.com/archives/253780

## 4. ባንኮችና የኢንሹራንስ ኩባንያዎች የኢንቨስትመንት ባንክ እንዲያቋቁሙ የሚፈቅድ መመርያ ፀደቀ

የኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ባለሙያዎች ማኅበር ዓርብ ሐምሌ 12 ቀን 2016 ዓ.ም. ባዘጋጀው 21ኛው የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ዓለም አቀፍ ኮንፈረንስ የተገኙት የካፒታል ገበያ ዋና ዳይሬክተር ብሩክ ታየ (ዶ/ር) እንደገለጹት፣ ብሔራዊ ባንክ፣ ባንኮችና የኢንሹራንስ ኩባንያዎች የኢንቨስትመንት ባንክ ማቋቋም የሚያስችላቸውን መመርያ አፅድቋል፡፡

**ሪፖርተር ጋዜጣ፡ *July 21, 2024***

መመርያው የኢንቨስትመንት ባንክ የሚያቋቁሙ ባንኮችና የኢንሹራንስ ኩባንያዎች የሚጣልባቸውን ገደቦች ማካተቱን የገለጹት ብሩክ (ዶ/ር)፣ ለዚህም ብሔራዊ ባንክ በጉዳዩ ላይ ትኩረት ሰጥቶ እየሠራበት መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

https://www.ethiopianreporter.com/131566/

## 5. በሆርቲካልቸር ዘርፍ 24 ቢሊዮን ዶላር በጀት የሚጠይቅ አገር አቀፍ ስትራቴጂ ይፋ ተደረገ

ከ2017 እስከ 2026 ዓ.ም. ድረስ ተፈጻሚ የሚሆነው ስትራቴጂ ስምንት ዋና ዋና ጉዳዮችን የያዘ ሲሆን፣ ስትራቴጂውን ለማዘጋጀት የግብርና ሚኒስቴርን ጨምሮ በሆርቲካልቸር ዕውቀት ያላቸው ምሁራንና የዘርፉ ተዋናዮች የተሳተፉ መሆናቸውን፣ ሐሙስ ሐምሌ 11 ቀን 2016 ዓ.ም. ሚኒስቴሩ ስትራቴጂውን ይፋ ሲያደርግ አስታውቋል፡፡

**ሪፖርተር ጋዜጣ፡ *July 21, 2024***

ከዚህ በፊት የነበረው ስትራቴጂ የግል ባለሀብቶች የሚያነሷቸውን ጥያቄዎች መልስ የማይመልሱ የተለያዩ የአሠራር ዘዴዎችን ባለማካተቱ፣ የሆርቲካልቸር ዘርፍ ስትራቴጂን እንደ አዲስ መከለስ አስፈላጊ መሆኑን፣ የግብርና ሚኒስቴር የእርሻና ሆርቲካልቸር ዘርፍ ሚኒስትር ደኤታ መለስ መኮንን (ዶ/ር) ተናግረዋል፡፡

**https://www.ethiopianreporter.com/131563/**

## 6. አየር መንገዱ የጉዞ ትኬታቸውን በኢትዮጵያ የሚገዙ የውጭ ዜጎች በውጭ ምንዛሬ መክፈል እንዳለባቸው አስታወቀ

አየር መንገዱ ጉዳዩን አስመልክቶ ባወጣው ማብራሪያ፥ ለመንገደኞች የሚሰጠውን ዓለም አቀፍ የበረራ ቲኬት ሽያጭ አገልግሎቶች በሙሉ በውጪ ምንዛሪ ብቻ እንደሚሆን ተደርጎ በተለያዩ የማህበራዊ መገናኛ አውታሮች ሲዘዋወር መመልከቱን አንስቷል፡፡

**ፋና፡ ሐምሌ 10፣ 2016**

ይሁን እንጂ የጉዳዩ ትክክለኛ መረጃ በቅርቡ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ የውጭ ምንዛሬ አጠቃቀም መመርያ ማውጣቱን ተከትሎ አየር መንገዱ ከውጪ ወደ ኢትዮጵያ ለሚደረጉ ጉዞዎች በሀገር ውስጥ መገበያያ ገንዘብ ሲሰጥ የነበረውን የቲኬት ሽያጭ አሰራር ከሐምሌ 2 ቀን 2016 ዓ.ም ጀምሮ በከፊል የተከለከለ መሆኑን አረጋግጧል፡፡

https://www.fanabc.com/archives/253908

### 7. ኢትዮ ቴሌኮም በአክሲዮን ተዋቅሮ እንደገና ሊቋቋም ነው

ኢትዮ ቴሌኮም በቅርቡ ሥራ ይጀምራል ተብሎ በሚጠበቀው የኢትዮጵያ መዋዕለ ንዋይ ገበያ (Ethiopian Securities Exchange) አማካይነት አሥር በመቶ ድርሻውን ለኢትዮጵያውያን እንደሚሸጥ፣ ጠቅላይ ሚኒስትር ዓብይ አህመድ (ዶ/ር)ን ጨምሮ ሌሎች ጉዳዩ የሚመለከታቸው ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣናት በተደጋጋሚ በይፋ መናገራቸው ይታወሳል።

***ሪፖርተር ጋዜጣ፡ July 14, 2024***

ይህንን በተመለከተ ሪፖርተር ያነጋገራቸው የኢትዮ ቴሌኮም ዋና ሥራ አስፈጻሚ ወ/ሪት ፍሬሕይወት ታምሩ፣ የኢትዮ ቴሌኮምን አሥር በመቶ ድርሻ ለመሸጥ ሲደረግ የነበረው ዝግጅት መጠናቀቁን ገልጸዋል። የኩባንያው አጠቃላይ ሀብት ግመታ (Asset Valuation) ስሙን ከመግለጽ በተቆጠቡት አንድ የውጭ ኩባንያ ተሠርቶ መጠናቀቁን ተናግረው፣ ‹‹በጣም በቅርብ ጊዜ ውስጥ›› አሥር በመቶ ድርሻው ለሽያጭ ይቀርባል ብለዋል።

https://www.ethiopianreporter.com/131355/

## *በውጭ ቋንቋዎችና ከውጭ ሚዲያዎች*

### 8. Debt Relief Initiative Should Be Scaled Up at Multilateral, Bilateral Frameworks: FM Taye

Ethiopian Foreign Minister Taye Atske Selassie said debt relief initiative should be scaled up both at multilateral and bilateral frameworks to solve unsustainable debt burden as well as unlock investment to SDGs.

**Ethiopian news agency: June 22/2024**

The opening session of the Preparatory Committee for the Fourth International Conference on Financing for Development (FfD4), which will be running until 26th July 2024, kicked off today in Addis Ababa.

https://www.ena.et/web/eng/w/eng_4825865

### 9. NBE approves directive allowing banks to invest 25% of capital in commercial ventures

The National Bank of Ethiopia (NBE), which regulates the financial industry, has ratified a new directive that allows banks to allocate 25% of their capital to other commercial ventures.

According to the revised 2017 'Limitation on Investment of Banks' Directive No SBB/65/2017, banks can now allocate a quarter of their total capital to other businesses, such as the insurance industry and capital market services.

**Capital Ethiopia-July 22, 2024**

The new NBE directive, primarily intended to enable banks to form subsidiary companies, states that any bank can acquire up to 100% equity shares in a capital market service provider, excluding credit rating agencies, as per Capital Market Proclamation No.1248/2021.

https://www.capitalethiopia.com/2024/07/22/nbe-approves-directive-allowing-banks-to-invest-25-of-capital-in-

### 10. Microsoft IT outage: Air travel, media, financial, telecoms hit by global cyber failure

A global tech outage was disrupting operations in multiple industries on Friday, with airlines halting flights, some broadcasters off-air and everything from banking to healthcare hit by system problems.

**THE EAST AFRICAN: JULY 19 2024**

Air passengers around the world faced delays, cancellations and problems checking in as airports and airlines were caught up in the massive IT outage.

https://www.theeastafrican.co.ke/tea/business/microsoft-it-global-outage-4695608

### 11. Washington to host African Trade ministers for AGOA in July

US President Joe Biden's administration will host trade ministers from developing countries in Washington DC next week to discuss plans to extend the African Growth and Opportunity Act (Agoa) until 2041.

Ambassador Katherine Tai, United States Trade Representative, announced that her country will host the 21st US-Sub-Saharan Africa Trade and Economic Cooperation Forum (Agoa Forum) in Washington DC from July 24 to 26.

**THE EAST AFRICAN: JULY 17 2024**

The ministerial programme will feature plenary sessions on the present and future of Agoa and US-Africa trade and investment cooperation, as well as breakout sessions on a variety of topics.

https://www.theeastafrican.co.ke/tea/business/washington-to-host-african-trade-ministers-for-agoa-4693086

### 12. Hotels reinstate full US dollar payments for foreign nationals

In a significant development, hotels across Ethiopia have restarted accepting full payment in US dollars from foreign passport holders for the services they provide.

**Capital Ethiopia-July 22, 2024**

This move comes after the National Bank of Ethiopia (NBE) has reinstituted a directive that had been in place previously, but had fallen by the wayside in recent years due to lax enforcement.

Aster Solomon, the president of the Addis Ababa Hotels Association, explained to Capital that the directive allowing hotels to collect service fees in US dollars from foreign nationals has been on the books for years. However, the lack of stringent control by the authorities had led to a loosening of the implementation.

https://www.capitalethiopia.com/2024/07/22/hotels-reinstate-full-us-dollar-payments-for-foreign-nationals/